ቁጥር ___ አ1162/11/551 ___

ቀን ሚያዝያ 05 ቀን 2014 ዓ.ም.

**ለኢትዮጵያ ዜጎች ለማሕበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)**

**አዲስ አበባ፣**

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማሕበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ መስከረም 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄዱንና የፓርቲውን ደንብ ማሻሻሉን ገልፆ ሪፖርት አቅርቧል።

የቀረበውን ሪፖርት እና ሠነዶች ከኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንፃር በመመርመር ያልተሟሉ ጉዳዮችን አሟልቶ እንዲያቀርብ ቦርዱ ኅዳር 3 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቆ ፓርቲው በበኩሉ ታህሳስ 16 ቀን 2014 ዓ.ም.፣ የካቲት 11 ቀን 2014 ዓ.ም. እና መጋቢት 7 ቀን 2014 ዓ.ም. በተፃፉ ደብዳቤዎች ምላሽ ሰጥቷል።

ቦርዱ መጋቢት 9 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ያቀረባቸውን ሰነዶች መርምሮ በአጠቃላይ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 4.2.6 መሠረት መተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው በጠቅላላ ጉባኤው በመሆኑ ፓርቲው መስከረም 22/2014 ያሻሻለው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ላይ ያሉ ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ጋር የሚቃረኑ አንቀፆች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤው በቀጣይ ስብሰባው አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግባቸው ወስኗል። በዚሁ መሠረት፡-

1. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ምዕራፍ 2

> ***" . . . በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የፓርቲው አካላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ነው። በልዩ ሁኔታ በሥራ አስፈጻሚው 2/3 ውሳኔ ለ3ወር ሊራዘም ይችላል። ለሁለተኛ 3 ወር ለማራዘም፤ የሀ/ተ/አ/ኮን ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል።"***



አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

የሚለው ከአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 1 /ሸ/ የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባዔም አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግበት፤

2. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 4.1.1 እና 18.6.2

> *" የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ፓርቲው መዋቅር ከዘረጋባቸው የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ 800 በድምጽ እና ሌሎች ያለድምጽ የሚሳተፉ አባላት ይኖሩታል፤ ከግማሽ በላይ በድምጽ የሚሳተፉ ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል።"*

በማለት ተደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ከግማሽ በላይ ማለትም 400+1 ከተገኙ የጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ የሚያስቆጥር ሊሆን ነው። ይሁን እና በአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 1 /ሰ/ መሠረት የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ምልአተ ጉባኤ ቢያንስ 500 እንደሆነ የተደነገገ በመሆኑና ከሕጉ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባዔም አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግበት፤

3. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 4.2.11

> *"አስገዳጅ ሁኔታዎች መኖራቸውን ብ/ሥ/አ/ኮ ሲያምንበት የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ለ3 ወር ሊራዘም ይችላል፤ አስገዳጅ ሁኔታው ካልተቀረፈ በሀ/ተ/አ/ኮ ለሁለተኛ ዙር 3 ወር ሊራዘም ይችላል።"*

የሚለው በአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 1 /ሸ/ ከተቀመጠው የ3 ዓመት ገደብ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚ እንዳይሆን፤

4. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 6.2.23

> *"ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በቀጥታ በአባላት የሚመረጡ የፓርቲ መሪዎች፣ የጉባኤ ተመራጮች በማንኛውም ሁኔታ በሥራ ላይ*

*ካልሆኑ እስከ ቀጣይ ኮንፈረንስ/ጉባኤ ድረስ በብ/ሥ/አ/ኮ በጊዜያዊነት ይሰይማል።"*

የሚለው በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የፓርቲው መሪዎችን ሥራ አስፈፃሚው መተካቱ ከአዋጁ አንቀፅ 80 ጋር የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚ እንዳይሆን በቀጣዩ ጠቅላላ ጉባዔም አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግበት፤

5. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 4.2.6

*የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ መፈተሽ፣ ማሻሻልና የማፅደቅ ኃላፊነት የጠቅላላ ጉባኤው ነው። ይሁንና በደንቡ አንቀፅ 5.2.7 የፓርቲው ኮንፍረንስ "የሀገደንብ ማሻሻያዎችን እስከሚቀጥለው ጉባኤ በጊዜያዊነት ያጸድቃል"*

በሚል ተመልክቷል። ይህ ሁኔታ ጠቅላላ ጉባኤው በሚሰበሰብበት ጊዜ ሊከልሳቸው ወይም ወደ ኋላ ሊመልሳቸው የማይችላቸው መሰረታዊ ማሻሻያንም ሊያከትት ስለሚችል፣ ይህ ደግሞ የጠቅላላ ጉባዔው ያለውን ደንብ የማሻሻል የመጨረሻ ስልጣን በተግባር ለሌላ አካል መስጠትን ስለሚያመጣ የፓርቲው ኮንፍረንስ ሊያሻሽል የሚችላቸው ጉዳዮች በዝርዝር ሊቀመጡ የሚገባ መሆኑን፤

6. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 7.1.1

*"የፓርቲው መሪና ምክትል መሪ በጣምራ በሁሉም የፓርቲው አባላት በአንድ ሰው አንድ ድምጽ የምርጫ መርህ በቀጥታ ይመረጣሉ።. . ."*

የሚለው በአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገውን በመከተል ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልጽ፥ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጥር በሚሰጥ ድምፅ የሚመረጡ መሆኑን ከማረጋገጥ አኳያ ዝርዝር አፈጻጸሙን የሚያመለክቱ ተጨማሪ ድንጋጌዎች መካተት ያለባቸው ሲሆን፣ በተለይም በየደረጃው የምርጫው አስፈጻሚዎች የሚለዩበትን አግባብ፣ በደንቡ መሰረት የቀረቡ የእጩዎች ዝርዝር ለአባላት በሙሉ ስለሚገለጽበት ሁኔታ፣ በፓርቲው በየምርጫ ክልል

ጽ/ቤት የተመዘገቡ ለመምረጥ መብት ያላቸው አባላት ብዛት ከምርጫው በፊት ይፋ ስለሚሆንበት እና የምርጫው ውጤት ስለሚረጋገጥበት እንዲሁም ስለሚዳመርበት አግባብ በዝርዝር መደንገግ የሚገባ መሆኑን፤

7. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 7.3.4

*"የፓርቲው ሊቀመንበር ............ ተግባራቸውን በትክክል አልተወጡም ብሎ ሲያምን ከሥራ አስፈጻሚነት በማንሳት በሌላ ይተካል።"*

ይላል። ይሁንና ሊቀመንበሩ ስልጣናቸውን በአግባቡ ብቻ እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ገደብ መኖሩን የሚያሳይ ነጥብ ባለመያዙ ይኸው ተብራርቶ መገለፅ ያለበት መሆኑ፤

8. በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 10.2

*"የሀገ ደንብ ተርጓሚና አስፈፃሚ ኮሚቴ ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ከስነ ስርዓት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ይመለከታል።"*

ይላል። ይሁንና በአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 1 /ረ/ መሠረት የጥፋት አይነቶችና ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት እና የሥነምግባር እርምጃ በዝርዝር በመተዳደሪያ ደንቡ ያልተካተተ በመሆኑ ይህን የሚመለከት ማሻሻያ በጉባኤው መጽደቅ ያለበት መሆኑን፤

9. ምንም እንኳን ፓርቲው የሚኖረውን መዋቅር የሚያሳይ መመሪያ አጸድቆ ቢያቀርብም በአዋጁ አንቀፅ 74 ንዑስ አንቀፅ 1 /ቀ/ መሠረት የፓርቲው ቅርንጫፎች አወቃቀርና አሠራርን ጨምሮ የፓርቲው መዋቅራዊ አደረጃጀትና የስልጣን ተዋረድ በመተዳደሪያ ደንቡ መወሰን እንዳለበት ስለተደነገገ ይህንኑ የሚያሳይ አጠቃላይ አሰራሩ በደንቡ ተካቶ ማቅረብ ያለበት መሆኑ፤

10. በመጨረሻም በፓርቲ ውስጥ የአመራር ስልጣን በምርጫ መያዙን ከማረጋገጥ አንጻር በመተዳደሪያ ደንቡ በመረው እና ሊቀመንበሩ የሚሰየሙት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር በጠቅላላ ጉባኤ ከሚሰየሙት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ብዛት ያለመብለጣቸውን በስራ ሂደቱ ማረጋገጥ እንደሚገባው ወስኗል።

በመሆኑም ፓርቲው በቀጣይ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ ከላይ በተገለፀው መሠረት ማሻሻያዎችን አድርጎ ሪፖርት እንዲያቀርብ እያሳወቀ ቦርዱ ፓርቲው መስከረም 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ እና ያስተላለፋቸውን ውሳኔ የመዘገበ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

ከበጎ ምኞት ጋር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ

ግልባጭ፡-

- ለም/ሰብሳቢ ቢሮ
- ለፓርቲ ጉዳዮች ስራ ክፍል